<u>የረቡዕ ታህሳሥ 19 1998 ዓም ( ዴሴምበር 28 2005)</u>

## <u>የፍኖተ ዴሞክራሲ ሐተታ</u>

## <u>ህይወት ካበቃ ሀኪም ፍለጋ</u>

በኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ ሞቶ የተቀበረን ሥርዓት ነፍስ ለመዝራት፥ ዛሬ በየአቅጣጫው የሚደረገውን የአስቸኳይ የነፍስ አድን መሯሯጥ ስንታዘብ፥ የአላዓዛርን ከመቃብር መነሳት ለማስታወስ እንገደዳለን፡፡ የክርስትና ዕምነት ተከታዮች፥ የአላዓዛር ከመቃብር መነሳት፥ በክርስቶስ ኃይልና ሥልጣን ነው ብለው ቢያምኑም፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን፥ የሞተውን የወያኔን ሥርዓት ነፍስ ሊዘራበት የሚችል ምድራዊ ኃይል ይኖራል ብሎ አያምንም፡፡ ይህ ዘረኛ ሥርዓት፥ እየተጠራሞተና እየተፈራገጠ ግን ሊሰነብት ይችል ይሆናል፡፡ በደመ-ነፍሱ ሲፈራገጥ ደግሞ፥ ጉዳት አያደርስም ለማለት የሚቻል አይሆንም፡፡ እንዲያውም የቆሰለ አውሬ ነውና ግራ ቀኙን ሁሉን ልንከስ ልጨርስ ማለቱ መጠበቅ ያለበት ነው፡፡ ይህም በመሆኑ ነው ዛሬ፥ የተቀዋሚ ድርጅት መሪዎችን በወኅኒ ቤት የሚያሰቃያቸው፡፡ አባላትና ደጋፊዎቻቸውን የሚያሳድዳቸው፡፡ ሰላማዊውንም ሕዝብ ያታና እድሜ ሳይለይ በመጨፍጨፍ ላይ የሚገኘው፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ፥ መለስና ግብረአበሮቹ፥ ኅልቆ መሳፍርት የሀገሪቱን ኃብትና ንብረት በማሸሽ ላይ ናቸው፡፡ የወያኔን የመጨረሻ አወዳደቅ፥ከመንግሥቱ ኃይለማርያም አወዳደቅ የሚለየው አንዱ ዓቢይ ነጥብ፥ መለስና ግብረ-አበሮቹ፥ መሸሻቸውን አስቀድመው አውቀው እንዴት እንደሚያመልጡ ዕቅድ ያላቸው መሆኑ ነው፡፡ የአጥፍቶ መጥፋት ዕቅድ ያላቸው መሆኑ ቢታወቅም፥ ከተሳካላቸው ያሸሹትን የኢትዮጵያ ሕዝብ ሀብት እስከ ዕድሜ ልካቸው ለመጠቀም የሚያስችላቸውን ሀገርና ሁኔታ አያመቻቹም አይባልም፡፡ አስቀድመው በገንዘብ የገዟቸው ወዳጆቻቸው በጊዚያዊነትም ቢሆን ሊተባበሩላቸው ይችሉ ይሆናል፡፡ ዘረኛ ሥርዓታቸውን ግን ከመደምሰስ ከቶ አያድኑትም፡፡

በመሠረቱ የማንኛውም ሀገር ሕዝብ የራሱን ዕድል መወሰን ያለበት እርሱ እራሱ መሆኑ ባይካድም፤ እናም ደግሞ፥ የኢትዮጵያ ሕዝብም በታሪኩ ከመጀመሪያው እስከ አሁን ድረስ የራሱ ታሪክ ፥ ሀገርና ነፃነት ወሳኝና አስከባሪ እራሱ ባለቤቱ እንደነበር ቢታወቅም፥ አሁን ግን የራሱና የሀገሩ ባለቤት አልሆነም፡፡ ዛሬ የኢትዮጵያ ሕዝብ ምዕራባውያን ያመጡበት አሻንጉሊት መንግሥት ስለተጫነበት፥ የውስጥ ፖለቲካውም ሆነ የውጭ ፖሊሲው የባዕዳንን ጥቅም በሚያስጠብቁ ቅጥረኞች ስር ወድቋል፡፡ ፖለቲካው የተመሰቃቀለ፥ የማኅበራዊው ኑሮ የተቃወሰ፥ኢኮኖሚው የተንኮታኮተ፥ የትምህርት አካሄዱ የተደናበረ፥ የውጭ ፖሊሲው የሀገርን ሉዓላዊነት ያስደፈረና ያዋረደ የሆነውም፥ ሀገር ወዳድ መሪዎች ባለመኖራቸው ነው፡፡ ሀገራችን በታሪኳ የነበሯት መንግሥታትና መሪዎች፥ አምባገነኖች ቢሆኑም የሀገርን ሉዋላዊነትና ብሔራዊ ጥቅምን ለበዕዳን በማስረከብ፥ እንደ አሁኑ ያህል ለውጭ ኃይል የተንበረከኩበትን ታሪክና ጊዜ መኖሩን ተጽፎ

አላነበብንም። አልተማርንምም። በአሁኑ ወቅት፥ የውጭ ባዕዳን፥ በኢትዮጵያ ጥቅማቸውን የሚያስጠብቅላቸው ተንበርካኪና ጉዳይ አስፈጻሚ ጎጠኛ ቡድን ስላስቀመጡ፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ አንቅሮ ቢተፋውም፥ በሥልጣን እንዲቆይላቸው በመረባረብ ላይ ናቸው። በሕዝቡ ዘንድ በፖለቲካ እንደ ሞተ የሚቆጠረውን ቡድን፥ ነፍስ ለመዝራት የሚሯሯጡትም፥ በዚህ ምክንያት ነው። በተለይ የሁለት ሀገሮች መንግሥታት ባለሥልጣኖች፥ መለስ ዜናዊን ከሞት አፋፍ ለማዳን የሚያደርጉትን የነፍስ አድን መሯሯጥ ለተመለከተ፥ ኢትዮጵያ ሀገራችንን ዘለዓለማዊ የእጅ አዙር ቅኝ ግዛታቸው ለማድረግ የወሰኑ መሆናቸውን ይገነዘባል። ለዚህ ዕቅዳቸውም ከመለስ ዜናዊ የበለጠ ተላላኪና ተንበርካኪ አያገኙም።

በኢትዮጵያ ውስጥ ዛሬ የሚፈፀመውን መንግሥታዊ ሽብርተኝነት በመቃወምና በማውገዝ መላው የዓለም ኅብረተሰብ፥ መንግሥታትና ድርጅቶች እንዲሁም የብዙ ሀገራት ፓርላማ አባሎች፥ አቋምና ውሳኔዎችን በማሳለፍ ላይ ናቸው። ለምሳሌ እንደ አውሮፓ ቀን አቆጣጠር በኖቨምበር 7 ቀን 2005 ዓም የተሰበሰበው የአውሮፓ ፓርላማ የወያኔ መሪዎች በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የሚያካሄዱትን ጭፍጨፋና የሰብዓዊ መብቶች ረገጣ አስመልክቶ ባለ 15 ነጥብ የያዘ የውግዘት ውሳኔዎችን አሳልፏል። ይህን በማድረጉም የኢትዮጵያን ሕዝብ ወለታና ምስጋና አትርፏል። እንደዚሁም በርካታ የአሜሪካ ኮንግሬስ አባላትና ሴናተሮችም ተመሳሳይ ውሳኔዎችን በማሳለፍ ላይ እንዳሉ፥ በተለያዩ መገናኛ ብዙኃን የሚወጡት ዜናዎች ያስረዳሉ።

ሁሉም በኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን እጅግ አሳሰቢና አደገኛ ሁኔታ በመግለጽ ለፕሬዝዳንት ጆርጅ ቡሽ ጠንካራ ደብዳቤ በመጻፍ፥ አሜሪካ በኢትዮጵያ ላይ ያላትን ፖሊሲ እንድትመረምር አሳስበዋል። ከዚህም በተጨማሪ፥ የአሜሪካ ፓርላማ የውጭ ግንኙነት ኮሚቴ ባሳለፈው ውስኔ ውስጥ፥ አሜሪካ፥ መለስ ዜናዊ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የሚያደርገውን ግፍ በአርምሞ ሳትመለከት ጣልቃ መግባት እንዳለባት የሚጠይቅ ውሳኔ ማሳለፉ ታውቋል። ክርስቶፈር ስሚዝ የተሰኙ ሌላ የአሜሪካ ምክር ቤት አባል ደግሞ፥ የስድስት መቶ ኢትዮጵያውያን ፊርማ ያለበት የተማጽኖ ደብዳቤ እንደደረሳቸው አሳውቀዋል። ኢትዮያውያኑ ፊርማቸውን ያስተላለፉት፥ የአሜሪካ ሴኔት በኢትዮጵያ ላይ ያሳለፈውን ውሳኔ፥ ማለት <u>ኤች አር 4423</u> የተሰኘውም ውሳኔ በመደገፍ እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል። ይህ ሁሉ ውጤት ሊመዘገብ የበቃው በድርጅቶችና በልዩ ልዩ የአሜሪካ ግዛቶች የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን በሚያደርጉት ያልተቋረጠ የዲፕሎማቲክ ተግባር እንደሆነ መረሳት የለበትም። ይህ ጥረት በቀጣይነትና በተቀነባበረ መንገድ እንደሚደረግ ሁሉም ኢትዮጵያዊ አምኖበት ቆርጦ ተነስቷል። እዚህ ላይ ልናስታውስ የምንፈልገው፥ በአሜሪካና አውሮጳ ውስጥ ከሚገኙት ኢትዮጵያውያን ምሁራን መካከል፥ በዲፕሎማሲው ትግል የሚሳተፉት እጅግ መጠነኛ ቁጥር ያላቸው ብቻ እንደሆኑ ነው። እነኝህ ሀገር ወዳድና የሕዝብ ተቆርቋሪ ምሁራን ጥረት እሰካሁን ድረስ ያስመዘገበው ውጤት የተሳካ ነበር ማለት የሚቻል ይመስለናል። እስካሁን ድረስ የተባ እንቅስቃሴ ያላደረጉ ምሁራን ሀገራችንን ከዘረኞች ለማዳን በሚደረገው

*በማነኛው የትግል ዓይነትና መስክ እንደሚሳተፉ÷የሁሉም ኢትዮጵያውያን የጋለ ተስፋና ምኞት ነው:: ለብሔራዊ ነፃነት ትግል ሁሉም የበኩሉን ድርሻ መወጣት እንደሚኖርበት የሚያጠያይቅ አይሆንም::*

*በዚህ ረገድ÷በአውሮፓ የሚገኙት ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን ያደረጉት ትግልና ያስመዘገቡት ዲፕሎማሲያዊ ውጤት ወገንን የሚያኮራ ብቻ ሳይሆን÷ መልካም አርዓያነቱ ሳይጠቀስ የሚታለፍ አይሆንም:: የአውሮፓ ፓርላማ ባለ አስራ አምስት ነጥብ ውሳኔ እንዲያሳለፍ የተገደደው÷ በድርጅቶችና አውሮፓ ባሉት ኢትዮጵያውያን የተቀነባበረና ያልተቋረጠ የዲፕሎማሲ ትግል መሆኑ ሁሉም ያውቀዋል:: በመካከለኛው ምሥራቅ የተለያዩ የዐረብ ሀገሮችና በእስራኤል የሚኖሩት ኢትዮጵያውያን/ያት የሚያደርጉት እንቅስቃሴም ተመዝግቧል:: በደቡብ አፍሪካ ÷ በአውስትራሊያ÷ በተለይም በሲዲኔ÷ በካምቤራና በሜልቦርን የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና በኒውዚላንድ ያሉት ወገኖቻችን የሚሰሩት ዲፕሎማሲያዊ ተግባር÷ ሀገር ቤት ለሚታገለው ሕዝብ የወገን አለኝታ ሆኗል:: የካናዳ መንግሥትና ፓርላማ የወሰዱት አቋምና ውሳኔ የተገኘው በካናዳ በሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን ከፍተኛ የዲፕሎማሲ እንቅስቃሴ መሆኑ ሳይጠቀስ የሚታለፍ አይደለም::*

*ለዴሞክራሲና ሀገርን ለማዳን የሚደረገው ትግል በውስጥና በውጭ ተጠናክሮ በመካሄድ ላይ መሆኑ የሚያበረታታና የነፃነታችንን ቀን መቃረቡን የሚያበስር ቢሆንም÷ ወያኔን ወደ መጨረሻ ሽንፈቱ ለመውሰድ ገና አልተቻለም:: የኢትዮጵያ ልጆች በውጭ በውስጥም ያሉት ተባብረው ሀገራቸውን ማዳን ቅድሚያ የሚሰጠው ብሔራዊ የትግል አጀንዳ ከሆነ ቆይቷል:: ይህ ከሆነ ዘንዳ÷ ውጤት እንዳናገኝ አንድ ወይም ሌሎች የጎደለን ነገር/ነገሮች አለ/አሉ ማለት ነው::* <u>*ታዲያ ያ ምንድን ነው?*</u> *በእኛ ዕምነት የሚከተሉትን ሁኔታዎች በግንዛቤ ውስጥ ማስገባት ያለብን ይመስለናል::*

1) *ከሁሉ አስቀድሞ÷ በእያንዳንዳችንም ይሁን÷ በድርጅቶች መካከል ብሔራዊ ዕርቅና ስምምነት ማስፈለጉ ወሳኝና አንገብጋቢ መሆኑ የሁሉም ሰው ዕምነት ሆኗል::* <u>*መቻቻል÷ መግባባት÷ መደማመጥ÷ መተማመንና መከባበር ከሌለ የጋራ ብሔራዊ አጀንዳ ነድፎ ሀገራዊ ትግል ማካሄድ አይቻልም::*</u> *ዛሬ ይህ መሠረታዊ ጉዳይ ባለመኖሩ ነው ትግላችን ሁሉ የመጨረሻ ግቡን ያልመታው:: የጋራ ሀገርን በጋራ ትግል ማዳን ካልተቻለ÷ የዲፕሎማሲውም ይሁን ሌላው ጥረት ብቻውን አይበቃም:: ብሔራዊ ዕርቅንና ሀገራዊ የጋራ የትግል አጀንዳ ነድፎ ለመታገል÷ ምሁራን÷ አዛውንት÷ የሃይማኖት አባቶች÷ ሴቶችና ወጣቶች ወሳኝ ሚና ሊጫወቱ ይገባል:: በሀገር ጉዳይ ማንም የዳር ተመልካች ሊሆን አይችልም:: ሁሉም ያልተሳተፈባት ኢትዮጵያ የተሟላች ሀገር መሆኗ ያጠራጥራል:: በመሆኑም ሁሉን ያቀፈ÷ ያስተባበረና ያካተተ ትግል ማካሄድ÷ የድል ዋስትና ብቻ ሳይሆን÷ ለወደፊቷ ኢትዮጵያ አንድነት÷ ዴሞክራሲያዊ ሂደትና ለፈጣን ዕድገት እንቅስቃሴ መሠረት ነው::*

2) አሁንም ተደጋግሞ ተደጋግሞ እየተነገረ ገና ምላሽ የላገኘው ጉዳይ፥ የጋራ ብሔራዊ አጀንዳ ኖሮ ያንን በተግባር የሚተረጉም ጠንካራ የተቃዋሚ ድርጅቶች ኃይል ወይም ማዕከል ዕውን አለመሆኑ ነው፡፡ የተቃዋሚ ድርጅቶች ጠንካራ ኅብረት መፈጠር አሁንም በኢትዮጵያ የፖለቲካ መልከአ-ምድር ቁልፍና ወሳኝ ጥያቄ ነው፡፡ ይህ ጥያቄ በአፋጣኝ ምላሽ ማግኘት የሚገባው ነው፡፡ ይዋል ይደር የሚባል አይደለም፡፡ ይህን ጥያቄ ደግሞ መመለስ ያለባቸው የፖለቲካ ድርጅቶች ብቻ ሳይሆኑ መላው የኅብረተ ስብ አባላትም ጭምር ናቸው፡፡ በዚህ ጥያቄ ላይ <u>የኢትዮጵያ ምሁራን የተለየ ኃላፊነትና ተግባር እንዳላቸው አንዳንዶቹ እስካሁን የተገነዘቡት አይመስልም፡፡</u> እያንዳንዱ ምሁር ሀገሩን ከወደቀችበት ለማዳን በሚደረገው ጥረት ምን እያደረግሁ ነው? ብሎ ኅሊናውን መጠየቅ ያለበት ይመስለናል፡፡ የራስን ኅሊና የመጠየቅ ጉዳይ ግን በምሁራን ብቻ የሚወሰን ሳይሆን፥ ሁሉም ዜጋ ሊቆጠቁጠው ይገባል ማለትን እንፈልጋለን፡፡

3) የዓለም ኅብረተስብ፥ ድርጅቶችና መንግሥታት በወያኔ ላይ ምንም ያህል ተቃውሞና ውግዘት ቢያዥጎደጉዱም፥ የኢኮኖሚና የዲፕሎማቲክ ማዕቀብ ቢያደርጉም፥ ምናልባት ለትግሉ እገዛ ያደርጉ እንደሁ እንጅ፥ የመጨረሻውን ድል ሊያስመዘግብ የሚችለው፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ የተባበረ ትግል መሆኑን ልንዘነጋው አይገባም፡፡ የራሳችንን ሀገርና ነፃነት ልናስከብርና ልናስገኝ የምንችለው እኛው ኢትዮጵያውያን ብቻ ነን፡፡ኢትዮጵያ በታሪኳም የቆየችው በዜጎቿ ኅብረትና የአንድነት ተጋድሎ ብቻ ነበር፡፡ ዛሬም የሀገራችንን ልዕልናም ይሁን ነፃነት የሚያስገኙልን ባዕዳን ሳይሆኑ፥ እኛው ነን፡፡ መስዋዕት ካስፈለገም ይህንኑ መክፈል የዜግነት ግዴታችን ነው፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብና መላው የዓለም ኅብረተስብ የጠላውንና ያወገዘውን የመለስ ዜናዊን ዘረኛ ሥርዓት የሁለት ባዕዳን መንግሥታት ፥ የነፍስ አድን መሯሯጥና ጥረት ከመጨረሻ ውድቀቱ ሊያድነው እንደማይችል፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ በዕርግጠኝነት መናገር ይችላል፡፡ ነባቢትን ወደ ተግባር ለመለወጥ ግን፥ የተባበረና የጠነከረ ሕዝባዊ ትግል ማስፈለጉ የሚያጠያይቅ አይደለም፡፡

ስለዚህም ወያኔን የባዕዳን ድጋፍ ለማሳጣት ትግላችንን እያፋፋምን ዋናው ተልዕኮ ግን ዜጎች ራሳችን የመለስን አገዛዝ ለመጣል ማካሄድ ያለብን ትግል ላይ ማተኮር መሆኑን መዘንጋት የለብንም፡፡